# <u>በልጅነቴ</u>

(ለእናቴ እመት ገላ ጎሹ ማስታዎሻ)

ታኅሣሥ 2004 ዓ.ም.
ከሊ. ማ. አበባው ይግዛው
ሎንዶን

ትዝታው መጣብኝ የህፃንነቴ፣
እስኪ ላጫውታችሁ አዳምጡኝ በሞቴ።

1. ነፍስ ሳውቅ የማውቀው ገና ከጅምሩ፣
   ውል አልኝ እየሱስ የደብረታቦሩ፤
   በጉም ተሸፍኖ ከራሱ እስተግሩ።
   ተጀንኖ ታየኝ፤ ሲያየን አቆልቁሎ፣
   እንደ <u>አለቃ ፀሐይ</u>[1] ጥምጥሙን ቆልሎ።
   ትዝ አለኝ እየሱስ የልደት ሲከበር፣
   <u>አንፈራጹ</u>[2] ሲባል ደብቴ ሲወዳደር።
   የተክሌው አቋቋም ዝማሜው መጣብኝ፣
   <u>መምሕር ወልደኪዳን</u>[3] ዝማሬውን ሲቃኝ፣
   "ርዕይዎ ኖሎት" እያለ ተሰማኝ።
   የተክሌው አቋቋም ትልቁ ምሥክር፣
   <u>ቀለመወርቅ ይማም</u>[4] ዘንግ ሲዎረውር፣
   ወደላይ አጉኖ፣ ሽቅብ አሽቀንጥሮ፣
   መልሶ ሲይዘው እንደ እንዝርት አሹሮ፣
   ትንግርት ነበረ ላዬው አተኩሮ።

ደብረ ታቦርና ጉና ሲነፃፀር፣
ታቦር አረሞኒዬም፣ አርሞኒዬም ታቦር።

ልጅነቴ ልጅነቴ፣
ማርና ወተቴ።

2. መድኃኔዓለም ደብር፣ ከደብረታቦሩ፣
   ፊደል ያስቆጠሩን አባቶች ነበሩ።
   <u>ከየኔታ መርሻ</u>[5] <u>ከየኔታ አዘዘ</u>[6]፣
   ያን ጊዜ ማን ነበር፣ ፊደል ያልቆጠረ፣ ሀን፣ ለን ያላጋዘ?
   ግዕዝ፣ ውርድ ንባብ፣ ቁም ንባብ ጨርሶ፣

---

[1] አለቃ ፀሐይ፦ የደብረ ታቦር እየሱስ አለቃ የነበሩና ትልቅ ጥምጥም የነበራቸው ካህን ነበሩ።

[2] "አንፈራጹ" "አንፈራጹ ሰብአ ሰገል፣ እምሀሑሙ አምፅኡ ገሐደ" (ሰብአ ሰገል ፈነደቁ፤ እጅመንሻቸውን በገሐድ አቀረቡ።) የሚለው የልደት በዓል ወረብ (ዝማሬ) ነው።

[3] መምሕር ወልደኪዳን፦ በጣም ጉልህ ድምፅ የነበራቸው የደብረታቦር መርጌታ ነበሩ።

[4] ቀለመወርቅ ይማም፦ የተክሌ አቋቋም ምሥክር፣ በኋላ መልአከ ታቦር ተብለው የደብሩ አለቃ የነበሩ።

[5] አባ መርሻ፦ የታወቁ የፊደልና የንባብ መምህር። ከአባ መርሻ ፊደል ያልቆጠረ የአካባቢው ሕፃን አልነበረም።

[6] የኔታ አዘዘ፦ የደብረታቦር መድኃኔዓለም መርጌታ ነበሩ፤ የሚታወቁትም መርጌታ አዘዘ ተብለው ነው። ንባብና ዜማ ያስተምሩ ነበር።

ዳዊት የደገመ መላልሶ መላልሶ፣
ይመረቅ ነበረ አዲስ ልብስ ለብሶ።
ሲያስተምሩን ውለን ትምህርት ሲፈታ፣
እንጸልይ ነበር ለነመምህር - ጌታ።
"እንደጨረቃ ያድምቅዎ!
እንደዋርካ ያስፋዎ!
እንደቄጠማ (ሠርዶ፣ ችብሐ) ያለምልምዎ!
በየኔታ ጉሮሮ ጠጅ ይንቆርቆር፤
በእኔ ጉሮሮ አጥንት ይሠንቀር።
ሆርነ እግዚኦ፣ ሆርነ እግዞኦ!" በለን፣
በተራ በተራ ጫማቸውን ስመን፣
"ሑሩ በሰለም" እንባላለን።
እኛም እየፈነደቅን ስንመለስ፣
ለመክሰሳችን እየሮጥን ተሽቀዳድመን ስንደርስ፣
ትዝ ይለኛል ያ ልጅነቴ፣
ጣፋጩ ጊዜ፣ ማርና ወተቴ።
የቀደስሁበቱ የተቀኘሁበት፣
ሰሞነኛ ሆኜ ያገለገልሁበት፣
እነ አለቃ ጌጤ[7] ደረት እየደቁ የተማፀኑበት፣
ባህታዊ ኃይሌ[8]፣ ውዳሴ ማርያሙን፣ የፈተቱበት፣
ደብረ - መድኃኔዓለም ትዝ አለኝ እንደ እናት።
እንኳንስ ቅዳሴው፣ እንኳንስ ማሕሌቱ፣
ያ ትልቁ ደወል[9] ትዝ ይላል ቅኝቱ።
ትዝ አለኝ መጣብኝ የትስብእቱ በዓል፣
በላይ ቤት በታች ቤት የጎንደር ይትበሃል፣
የነአለቃ ኃይሌ ጽናጽል አጣጣል፣
ትዝ አለኝ ወረቡ፣ ምልጣኑ ሲነሣ፣
"ነብሮ" የሚባለው ከበሮ ሲያገሣ።

3. አቡነ ሚካኤል እኒያ የግሼኑ፣
ደግ አባት ነበሩ፣ የተመሰገኑ።
አብሬ ቀድሼ፣ እኔም እድል ገጥሞኝ፣
ጀሮዬን እያሹ ወደቤት ወስደውኝ፣
ከዚህ ቆይ ተብዬ በማረፊያ እንዳለሁ፣
ወደእርሳቸው ክፍል ሲከፈት እያየሁ፣
ምግብ ሲመገቡ ድንገት ተመልክቼ፣
ሰው መሆናቸውን በፍፁም ዘንግቼ፣
አዕምሮዬ ዞረ፣ በጣም ደነገጥኩኝ፣
በዓይኔ ያየሁትን ለማመን አቃተኝ።

[7] አለቃ ጌጤ በጣም ደግ ከመደኃኔ ዓለም እድሞ ሥራቸው የማይለዩ፣ ደረታቸውን በድንጋይ እየገጩ የሚማፀኑ አለቃ ነበሩ።
[8] ባህታዊ ኃይሌ፦ ልጅም አዋቂም የሚወዳቸውና የሚያከብራቸው ዘግተው የሚኖሩ ባህታዊ ነበሩ። ለፍልሠታ ጾም ብቻ ወጥተው በቤተክርስቲያኑ የውዳሴ ማርያም ትርጉም ሲያሰሙ አይጠገቡም ነበር።
[9] ትልቁ ደወል፦ አፄ ቴዎድሮስ ደብረ ታቦር መድኃኔዓለምን ሲያሠሩ ከጎንደር አስመጥተውት ያገለግል የነበረ ደወል ነው። ድምፁ ከ50 - 60 ኪ/ሜትር ይሰማ ነበር። ለደዋይም ያስቸግር ነበር። በተለይ ለእኛ ለሕፃናቱ ዲያቆናት።

ክህነት የሚሰጡን አቡኑ ጳጳሱ፣
አይመስለኝም ነበር እህል የሚቀምሱ።
        የልጅቱ ማርያም ትላልቁ ጥዶች፣
        የሐጣ፣ የዝመሊ፣ የፈውስ ጠበሎች፣
        የእማሆይ አደላሁ የሰንበት ቂጣቸው፣
        የደንጎራው ኃይሌ፣ ግዙፍ ቁመታቸው፣
        የአባ ወንድሜነህ፣ መረዋ ድምፃቸው፣
        ሕልም ይሆንብኛል አሁን ሳስባቸው።
የእናቲቱ ማርያም፣ የጠጉር ሚካኤል፣ የእየሱስ ሥዕሎች፣
ብርቅ ድንቅ ነበሩ፤ የራስ ጉግሣ ቅርሶች፣
እነርሱን እያየሁ፣ ስለተመስጥሁኝ፣
ሥዕል እማር ነበር ጊዜ እየፈለግኩኝ።
ባለሃይማኖቱ አያወላውሌ፣
ብዙ ሥራ ሠርቷል ደጉ ጉግሣ ወሌ።
        ልጅነቴ ልጅነቴ፣
        ማርና ወተቴ!

4. ውል አለኝ መጣብኝ፣ የአጅባር[10] ትዝታ፣
   የጥምቀቱ  በዓል፣ የገናው ጨዋታ።
   በጥምቀተ ባሕሩ ታቦት ተሰልፎ፣
   የደብሩ ካህን፣ ታጥቆና አሰፍስፎ፣
   "ማዕከለ ባሕርን"[11] ሊቃውንት ሲቀኙ፣
   ሽብሸባው ሲጀምር፣ በበአሉ ቀለም፣ ደብተሮች ሲዋኙ፣
   ጥምቀት ልዩ ነበር የደብረታቦሩ።
   አስረጋጩን ቀድመው፣ ሽብሻቦ እየመሩ፣
   አለቃ ጥሩነህ[12] እንደ እንዝርት ሲሾሩ።
   የገናው ጨዋታ፣ የዘፈኑ እስክስታ፣
   "የአሲላ ገናዬ"[13] ዘለፋና ሆታ፣
   ውል ውል ይለኛል፣ የጥምቀት ጨዋታ።

          እነማሆይ ሁሉ ላሊበላን ስመው፣
          እንደተመለሱ፣ በረከት ተካፍለው፣
          እያቀነቀኑ ዘፈን መሃል ገብተው፣

[10] አጅባር፦ በደብረ ታቦር ከተማ ሚገኝ ትልቅ ሜዳ ነው። አፄ ቴዎድሮስ መጀመሪያ ድንኳናቸውን የተከሉበትና ልጃቸው ስደተኛው ልዑል ዓለማየሁ ቴዎድሮስም የተወለደው አጅባር ነው። ሰፊ ታሪክ አለው።
[11] "ማዕከለ ባሕር" "ሒዷኀ ተሥአ ወተሣተ ነገደ፤ ቆመ ማዕከለ ባሕር፣ ወወጽአ በሠላም" (ዘጠኙን ነገደ መላዕክት ትቶ በባሕር መካከል ቆመ፣ በሰላምም ወጣ የሚለው የጥምቀት ወረብ ነው።)
[12] አለቃ ጥሩነህ፦ በሽብሻቦ የታወቁ፣ የደብረታቦር እየሱስ አለቃና የክፍለ ሀገሩ ካህናት ቢትወደድ ነበሩ። መልካቸው፣ ካባቸውና አረማመዳቸው ሁሉ በጣም ደስ ይል ነበር።
[13] "አሲላ ገናዬ"፦ አሲላ በል፣ አሲላ ገናዬ እየተባለ በገናው ጨዋታ በተቸነፈው ቡድን ላይ የሚዜምበት ተራ ዘለፋም ያለበት ዘፈን ነው። ለምሳሌ፦ "ከወዲያ ከወዲህ ባመላልስበት፣
                    ኧረ አይዋ እነቶኔ.... ደረሰበት፡
                    ኧረ አይዋ እንቶኔ የ....  ባል፣
                    ልጅ ወልዳልሀለች ቀለቧን ሥፈር፣
                    አል____ ሁም ስትል ...ን ይዘህ ማል።
እና የመሳሰለውን ሲሉ ሰምቻለሁ።

ይወረወር ነበር፣ ጫንቃቸው፣ ጥላቸው፣
"ቅዱስ ላሊበላ፣ የላስታው ደብር፣
ውስጡ አረንጓዴ ነው ባሕር።
ውስጡ አረንጓዴ ነው ባሕር።
ወደ ላሊበላ ለሚሄዱ፣
አልጋ በአልጋ ነው መንገዱ።

(ከሴቶች)
ከዚያው ማርልኝ ያን ግትቻ፣
ከዚያው ማርልኝ ያን ግትቻ፣
ይገፎው እንዳልመጣ፣ አጥቼ ማንገቻ።
(ከወንዶች)
ከዚያው ማርልኝ ያችን እሳት፣
ከዚያው ማርልኝ ያችን እሳት፣
ያሦት እንዳልመጣ፣ ነገሩ አያደርሳት።"
እያሉ ግጥሞችን በዜማ ሲያወርዱ፣
ያስቀኑ ነበረ፣ ለሴቱም ለወንዱ።
በሆታ በልልታ ታቦቶች ሲሸኙ፣
በጣም ውል ይለኛል ሴት ወንድ ዘፋኙ።
አፄ ቴዎድሮስ ታላቁ ገናናው፣
አጅባር ላይ ነበረ፣ የመጀመሪያዋን ድንኳን የተከለው።
ከድንኳን ቀጥሎ ያንገት እዳ[14] እልፍኝ የተገነባበት፣
ልጅ ዓለማየሁም የተወለደበት፣
ዜናውን ለማብሰር መደፍ ያንቧረቀበት፣
የፈረሱ ግልቢያ፣ የገና ጨዋታው፣
ሌላም ብዙ ነገር የተከናወነው፣
በባለ ታሪኩ በአጅባር ሜዳ ላይ ነው፣
ምንጊዜም ትዝታው በማይደበዝዘው።
ልጅነቴ! ልጅነቴ!
ማርና ወተቴ።

5. ታየኝ ሰኞ ገበያ[15] የጥንቱ የጥዋቱ
ታናሹ ራስ አሊ ያሰቀረጡበቱ።
ወደሰኞ ገበያ ለመውጣት ለመውረድ፣
በሰባቱ አቅጣጫ፣ አለው ሰባት መንገድ፣
ታላቁ ገበያ ሁሉን አጠናቅር፣
ከወሎ፣ ከጎጃም ገበያተኞቹ ይውሉበት ነበር።
በሰኞ ገበያ ፍራፍሬ ሲያምረን፣

[14] ያንገት እዳ፦ የአፄ ቴዎድሮስ ቤተመንግሥት ስም ነው። ሥራው በጣም ያማረ በመሆኑ በአካባቢው የሚያልፈው ባላገር ሥራውን በማድነቅ ለብዙ ጊዜ አንጋጦ ሲመለከት አንገቱን ያመው ስለነበር "ያንገት እዳ" የሚል ስም አወጣለት።
[15] በክፍለ ሀገሩ ከሚታወቁት የጥንትና ታላላቅ ገበያዎች አንዱ ሲሆን የገበያተኛው የተደመረ ድምፅ እስከ ሃያ ኪሎ ሜትር ይሰማ ነበር። አዋጅ የሚነገርበት፣ ወንጀለኛ በግርፋትም ሆነ በስቅላት የሚቀጣበት መቀጣጫ ሥፍራ ነበር። ሁለቱንም አይቻለሁ።

የጨው - አይበላውን[16] አዘናግተን፣
ኮክ እንሰርቅ ነበር፣ አቅማዳ ጎትተን።
የሚሸጠውን ኮክ፣ ሜዳ ላይ በትነን።
    ገበያው ሲፈታ ሁሉም ሲበታተን፣
    የመንደሩ ልጆች ወዲያው ተጠቃቅሰን፣
    በየነጋዶቹ መደብ[17] ተሠማርተን፣
    እንፈልስ ነበር ቡና እየለቃቀምን።
    የተረሳም ዕቃ ለማግኘት እየጣርን።
        ልጅነቴ! ልጅነቴ!
        ማርና ወተቴ።

6. የህፃንነቴ ብዙ ትዝታ አለኝ፣
  ዘመኑ በዛና ለመምረጥ ተሳነኝ።
  ለእናቶቻችን የምግብ ማብሰያ፣
  እንጨት ስንለቅም፣ ሸለሸል[18] ፋንድያ፣
  ከታላቅ ወንድሜ ከጓደኞቹም ጋር፣
  ጫካ ተሠማርተን እንጨት ስንሠብር፣
  ዘፈኑ ጨዋታው እንዴት ያምር ነበር!
      ስሌወንዝን[19] አልፈን በቱሚ[20]፣ በጋጃ[21]፣
      ዘይንተረፍ ነበር የሰባው አምጃ[22]።
      አምጃውንና ደረቁን ቁራባ[23]፣
      አሰባስበን ይዘን ወደቤት ስንገባ፣
      ሸክሙን ስንጥለው ከበር አሸቀንጥረን፣
      "ቆንጆ ጣል!"[24] የሚል ምርቃት ነበረን።
በገንጨትም ሆነ በቄስ ፍሴ ጫካ፣
ጅግራውና ቆቁ እንደዚያ ሲያሽካካ፣
ነብር እንዳይበላን እንመክር ነበር፣
አሁን እንዴት ይሆን ደኑ ሲመነጠር?
በሃይቶኝ፣ በጀበል፣ በዲቃይ፣ በአውሊላ[25]፣

---

[16] ጨው አይበላ፡- ጨው ማለት በጎንደር የተደቆሰ በርበሬ (ድልህ) ማለት ነው። ከደብረ ታቦር ኢየሱስ በስተምዕራብ የሚገኘው ለምለም ቦታ በዚህ ስም የተሰየመው በጥንት ጊዜ በዚህ ቦታ ከወተት ተወፅዖ በስተቀር ጨው የማይበላ ሰው ይኖርበት ስለነበረ ነው። እዚህ ቦታ ኮክ በብዛት ይመረታል። የዚሁ የጨው አይበላ ገበሬ ሊሸጥ ያመጣ የነበረውን ኮክ ነው ኩታራው ይዘርፍ የነበረው።
[17] የነጋዶች መደብ፡- እያንዳንዱ ነጋዴ የሚነግድበት የዕቃው ማሣረፊያ መደብ አለው። ያንዱን ሌላው አይነካም፣ ይቀረጥበታል።
[18] ሸለሸል፡- የከብት እበት እንደወረደ በሜዳ ላይ ይደርቅና ያንን እየሰበሰብን ለማገዶ እንወስዳለን።
[19] ሰሌወንዝ፡- ለከተማው በጣም ቅርብ የሆነች የምንጭ ውሃ ስትሆን፣ በስተምሥራቅ በኩል ትገኛለች። አሁን ትኑር ትድረቅ አላውቅም።
[20] ቱሚ፡- መስኖ ውሃ ገብ ለምለም ቦታ ናት፤ እስተጋጃ ትዋሰናለች።
[21] ጋጃ፡- ከደብረ ታቦር ኢየሱስ ተራራ ግርጌ በስተ ምሥራቅ የሚገኝ ሰፊ ጫካ የነበረበት፣ ጅብ በቀን የሚጮህበት ቀበሌ ነበር።
[22] አምጃ፡- በሌላው ቦታ በቁጥቋጦ መልክ ነው የሚገኘው። በጋጃ ዱር ግን የሚፈለጥ የአምጃ እንጨትም ሞልቶ ነበር። ሆዳችን ቁርጠት ሲያመን የአምጃ ቀንበጥ በልተን እንድን ነበር።
[23] ቁራባ፡- ሰፋፊ ለምለም ቅጠል ያለው፣ ለመፍለጥ የማያስቸግርና ፍም የሚወጣው እንጨት ነው።
[24] "ቆንጆ ጣል" የእናት ምርቃት ነው። እንጨት ተሸክመን መጥተን ከበሩ ላይ ስንጥለው እናታችን ትወጣና "ቆንጆ ጣል" ትለናለች። ያሳድግህ፣ ለቆንጆ ሚስት ያብቅህ ማለት ነው። በዚያ አካባቢ የተለመደ ምርቃት ነው።
[25] ሐይቶኝ፣ ጀበል፣ ዲቃይ፣ አውሊላ፡- ከከተማው በስተምሥራቅ የሚገኙ የደንና የእርሻ ሥፍራዎችነበሩ። እኔ ከወንድሜ ጋር እንጨት የለቀምሁ በእነዚህ አካባቢዎች ነው። እስከሳባ ሚካኤልም እንወርድ ነበር።

ብዙ የዱር ፍሬ ነበር የሚበላ።
በተለይ በሃይቶች እንጨት ስንሠብር፣
የምንበላው ፍሬ በየዓይነቱ ነበር።
ኢጋምና ቀጋው፣ እንጆሪው ኮሽሙ፣
እንደልብ ነበር ለሚሽቀዳደሙ።
ሾላውና ቃሞው፣ እንጎችየው ሁሉ፣
ማንም አያልፋቸው ብሉኝ፣ ብሉኝ ሲሉ።
የእንጆሪውን ልምጫ[26] ያጋም የቀጋውን፣
ምንጭ እንወርድና፣ እሽት አርገን ጨምቀን፣
ሰፋፊውን ቅጠል እንደዋንጫ ሠርተን፣
እንጠጣው ነበር እየተፎካከርን።
በጣም ደስ ይለኛል ሳስታውሰው ያን ዘመን።

ልጅነቴ! ልጅነቴ!
ማርና ወተቴ።

7. በህፃንነቴ ካሳለፍኩት ሁሉ፣
ብዙ ጨዋታዎች ትዝ የሚሉኝ አሉ።
እኔ ከማውቃቸው ጨዋታዎች ዝርዝር፣
የትግል ጨዋታ ያስቸግረኝ ነበር።
በትግል ጨዋታ እንደማስታውሰው፣
ምልቃ መግባትና መዘርጠጥ ክልክል ነው።
የሰኞ ገበያው አባባ ተሻለ፣
በጫኝውሃ ሜዳ ልጅ እያታገለ፣
ይሸልም ነበረ በስልት ለጣለ።
በሰኞ ገበያ፣ በኛ በመንደሩ፣
በቁም የሚያፈርጡ ታጋዮች ነበሩ።
ለገና ጨዋታ ገና ስንዘጋጅ፣
ለገናው ጨዋታው እሩር ስናዘጋጅ፣ ጥንግ[27] ስናዘጋጅ፣
ከወዲያ ከወዲህ ቡድን ስናቀናጅ፣
በዋናው ጨዋታም ሲሞቅ ውድድሩ፣
ሁሉም ትዝ ይለኛል ለማልማት[28] (ለማግባት) ሲጥሩ፣
በትልቁ ሜዳ፣ በጥንቱ በአጅባሩ፣
ለም የሚለማበት ጥንጉም ሆነ ሩሩ፣
ሰሜንና ደቡብ ትላልቁ መንገድ፣ ነበረ ድንበሩ።
የተጫወትሁትን አሁን ሳስታውሰው፣
የበጋው ጨዋታ በርከት ያለ ነው።
አቀብሎ እሩጫ፣ ጉምብሶሽ፣ ቅልቦሹ፣
ቅንጭፍት፣ ተግር በታች፣ የድባ ቅጭቱ፣
ሁሉም ደንብ ነበረው ጥብቅ ነው ሥርዓቱ።
የባህሉ ጨዋታ ከአባት የወረስነው፣

[26] ልምጫ ወይም ሎምጫ፣ የበሰለ ፍሬ ማለት ነው። በተለይ ልምጫ ቀጋ ይባላል።
[27] ጥንግ፦ እንደ ኳስ ድቡልቡል ሆኖ ከቀጭን ጠፍር በዛብ ሥራ የተሠራ እሩር ወይም የገና መጫዎቻ ማለት ነው።
[28] ለማልማት፦ ጥንጓ ወይም ሩሯ የጨዋታውን ግብ ስታልፍ ለማች ይባላል። ግብ ማግባት ማለት ነው።

የኛ መዝናኛችን ትዝታው ብዙ ነው።
በመስከረም ወራት ክረምት ሲወጣልን፣
አጅባር ሜዳ ወርደን አሽንድዬ[29] ቆርጠን፣
መጠኑን ወስነን ባጫጭሩ ከትፈን፣
አጥንቱን አሹለን ወይም በጃርት እሾህ፣
በአካናዱራ[30] "ወጋሁህ፣ ወጋሁህ"
እንጫወት ነበር ከወዲያ ከወዲህ።
የሰኞ ማክሰኞ፣ ኪሣራም ጨዋታ፣
ያስደስተኝ ነበር ስረታ፣ ስረታ፣
የዋዛ አልነበርሁም በመምች ስመታ።
ክረምቱም ሲገባ በመንገድ ዳርቻ እያቦካን ጭቃ፣
እንተኩስ ነበር ቦምብና ባዙቃ።
ጭቃውን አልፍተን፣ እንደሙዳይ ሠርተን፣
መጋጠሚያውንም በጣም አለስልሰን፣
ገበያተኞቹ ከእኛ ዘንድ ሲደርሱ፣
እናኖጋው ነበር እስኪወጣ ጢሱ።
ገበያተኞቹም እየደነገጡ፣
ይራገሙ ነበር እርግማን ሳይመርጡ፤
አቤት የእኛ ደስታ! ኧረ ምኑ? ቅጡ።
ልጅነቴ! ልጅነቴ!
ማርና ወተቴ።

8. ትዝ አለኝ አራዳ፣ የመስቀሉ በዓል፣
ደመራው ሲለኮስ፣ ችቦው ሲቀጣጠል።
የእዮሐ - መብራቱን[31] ሁሉም አቀጣጥሎ፣
እዮሐ ! ይል ነበር በቡድን ተከፍሎ።
ፈረስ ግልቢያው ሲደምቅ፣ ጋላቢ ሲሞቀው፣
ዘንጉን አነጣጥሮ በሌላው ሲለቀው፣
ደምቶም ተደብድቦም አልነበረም ቁጣ፤
የፈረስ ግልቢያው ባህል ካባት ስለመጣ።
የደመራው እሣት ረመጡ ሲቀር፣
ለምለም አረንጓዴ አሽክት[32] በመጨመር፣
እግር በሽተኛ ይታሽበት ነበር።
በደብረ ታቦርም በከተማዋ አቅም፣
እውነት የሚናገር እብድ ጠፍቶ አያውቅም።

[29] አሽንድዬ፡- ረግረግ ሜዳ ላይ በክረምት የሚበቅል ባለጥሩንባ አበባና ረጃጅም ቅጠል ያለው አበባ ነው። ቅጠሉን ሰቶቹም ታጥቀው "እቴ አበባዬን" ይዘፍኑበታል።

[30] አካናዱራ፡- ከጫዋታዎች ዓይነት አንዱ ነው። የአሽንድዬውን ጥሩንባ አበባ አገዳ ከትክተን፣ በሾለ አጥንት ወይም የጃርት እሾህ ወጋሁህ እያልን፣ በወጋነው ልክ እየቆጠርን እናሸንፋለን፤ ወይም እንሸነፋለን።

[31] እዮሐ - መብራት፡- በአዲስ አበባ ችቦ የሚባለው የመስቀል መብራት ነው። እዮሐ - አበባዬ ስለሚባል እዮሐ ብለውታል። አይሀ መብራት እንደማለት ነው።

[32] ለምለምና መሬት ለመሬት እየተሳበ የሚያድግ አረም የመሰለ ዕፅ ነው። ሴቶች ድንች ሲቀቅሉ በርሱ ሲሸፍኑት (ሲከድኑት) ቶሎ ይበስላል ይላሉ። ፈጥኖ ላቦት ያመጣል። የመስቀል ደመራ ደግሞ ከተቀጣጠለ በኋላ ረመጡ ሲቀር ኮርማ የተባለው የውስጥ እግር በሽታ ያለባቸው ሰዎች ያንን ይጎዘጉዙና በእግራቸው ጫማ ይቆሙበታል። ከአሽክቱ በሚወጣው ላቦት ይፈወሳሉ። በዙ ሰዎች በየዓመቱ እንደዚያ ያደርጉ ነበር።

እናውጋው ጀምበር፣ አልማው፣ እልል መንግሥት፣ ገሠሠች በሙሉ፣
ትዝ ትዝ ይለኛል ነገራቸው ሁሉ።
አባ ጥጋብ ጡሬም ከነወዘናቸው፣
ዛሬም ትዝ ይሉኛል ግጥማቸው ዜማቸው።
ልጅነቴ! ልጅነቴ!
ማርና ወተቴ።

9. የኔ ትዝታዬ የደብረ ታቦሩ፣
ማለቂያ የለውም ቢቆትሩ፣ ቢሠፍሩ።
አባታችን ሙቶ በጣም ተቸግራ፣
እኛን ለማሳደግ እጣነፍሷን[33] ጥራ፣
ደሐዋ እናታችን ያየችው መከራ፣
ይሰቀጥጠኛል አልችልም ላወራ።
ሽቀጥ ተሽክማ፣ አራዳ ሽቅጣ፣
በእውቅ ባልትናዋም የአሠር - ውሃ ሽጣ፣
ወንዶቹን ልጆቿን አስተምራናለች፣
በአርአያነቷ ዛሬም ታኮራለች።
እግዚኤር ነፍሷን ይማር፣ እኛን አስተምራ አገልግለዋለች።
ልጅነቴ! ልጅነቴ!
ማርና ወተቴ።

ዛሬ በዚህ ይብቃኝ፣ ሌላው ይቀጥላል፣
ትዝታ ሲበዛ ልብ ያነሆልላል።

[33] እጣነፍሷን፦ ማለት ብቻዋን፣ ያለምንም ረዳት ማለት ነው።